www.abyssinialaw.com

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፹
አዲስ አበባ–ሐምሌ ፫ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 80
ADDIS ABABA–10th July, 2003

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፱/፲፱፻፺፭ ዓ.ም
ፌዴራል መንግሥት በክልል ጣልቃ የሚገባበትን ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ...................... ገጽ ፪ሺ፪፻፲፮

## CONTENTS

Proclamation No. 359/2003
System for the Intervention of the Federal Government in the Regions Proclamation Page 2216

## አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፱/፲፱፻፺፭
## ፌዴራል መንግሥት በክልል ጣልቃ የሚገባበትን ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

በሕግ–መንግሥቱ አንቀጽ ፶፩(፩) መሠረት ፌዴራል መንግሥቱ ሕገ–መንግሥቱን የመጠበቅና የመከላከል ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጠው በመሆኑ፤

በሕገ–መንግሥቱ አንቀጽ ፶፩(፲፬) ከክልል አቅም በላይ የሆነ የፀጥታ መደፍረስ ሲያጋጥም በክልሉ መስተዳድር ጥያቄ መሠረት የፌዴራል መንግሥቱ የመከላከያ ኃይል እንደሚያሰማራ በመደንገጉ፤

በሕግ–መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭(፲፮) በማናቸውም ክልል ሰብዓዊ መብቶች ሲጣሱና ክልሉ ድርጊቱን ማቆም ሳይችል ሲቀር፤ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በራሱ አነሳሽነትና ያለክልሉ ፈቃድ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጋራ ስብሰባ ጥያቄ በማቅረብ ፣ በተደረሰበት ውሳኔ መሠረት ለክልሉ ምክር ቤት መመሪያ እንደሚሰጥ በመደንገጉ፤

በሕገ–መንግሥቱ አንቀጽ ፷፪(፱) ማናቸውም ክልል ሕገ–መንግሥቱን በመጣስ ሕገ–መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣለ እንደሆነ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ፌዴራል መንግሥቱ ጣልቃ እንዲገባ እንደሚያዝ የተደነገገ በመሆኑ፤

ከላይ የተጠቀሱትን የሕገ–መንግሥቱን ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት በሕግ መደንገግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ–መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

## *PROCLAMATION NO. 359/2003*
## *SYSTEM FOR THE INTERVENTION OF THE FEDERAL GOVERNMENT IN THE REGIONS*

WHEREAS, it is provided for in Article 51(1) of the Constitution that the Federal Government has power and responsibility to protect and defend the Constitution;

WHEREAS, it is provided for in Article 51(14) of the Constitution that the Federal Government deploy Defense forces at the request of State administration to arrest a deteriorating security situation within the requesting State when the Region is unable to arrest such situation;

WHEREAS, it is provided for in Article 55(16) of the Constitution that the House of Peoples' Representatives request, on its own initiative, a joint session of the House of the Federation and of the House of Peoples' Representatives to take appropriate measures when State authorities are unable to arrest violations of human rights within their jurisdiction, and give directives to the concerned Council of State;

WHEREAS, it is provided for in Article 62(9) of the constitution that the House of the Federation order the Federal intervention if any State, in violation of this Constitution, endangers the constitutional order;

WHEREAS, it has become necessary to prescribe by law the system that enable to implement the aforementioned provisions of the Constitution;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the constitution, of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.80

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

www.abyssinialaw.com



## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ፌዴራል መንግሥት በክልል ጣልቃ የሚገባበት ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፱/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· **ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ

፩· "ጣልቃ መግባት" ማለት በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፷፪(፱) መሠረት በክልሎች ጣልቃ የሚገባበት ሥርዓት ሲሆን በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፶፩(፲፬) ወይም አንቀጽ ፶፭(፲፮) መሠረት የሚወሰዱ እርምጃዎችን ይጨምራል፤

፪· "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

## ክፍል ሁለት
## በፀጥታ መደፍረስ ምክንያት ስለሚደረግ ጣልቃ ገብነት

፫· **መሠረቱ**

በአንድ ክልል ውስጥ የሕዝቡን ሰላምና ደኅንነት የሚያውክ እንቅስቃሴ ሲደረግና የተፈጠረውን የፀጥታ ችግር የክልሉ ሕግ አስከባሪ እና የዳኝነት አካል በሕጋዊ መንገድ ለመፈታት የማይችሉበት ሁኔታ ሲፈጠር የፀጥታ መደፍረስ እንደተፈጸመ ይቆጠራል ።

፬· **በክልሉ ስለሚቀርብ ጥያቄ**

ማናቸውም ክልል በራሱ ኃይል ሊቋቋመው የማይችለው የፀጥታ መደፍረስ ያጋጠመው እንደሆነ የክልሉ ምክር ቤት ወይም የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በኩል ጥያቄውን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀርባል ።

፭· **በፌዴራል መንግሥቱ ስለሚሠማራው ኃይል**

፩· ጠቅላይ ሚኒስትሩ የፀጥታውን መደፍረስ ለመቆጣጠር እንደ ችግሩ ክብደት የፌዴራል ፖሊስ ወይም የመከላከያ ሠራዊት ኃይልን ወይም ሁለቱንም ያሠማራል ። የሚሠማራው ኃይል በሚመለከተው የፌዴራል መንግሥት አካል የሚታዘዝ ይሆናል ፤

፪· የሚሠማራው ኃይልና በኃይሉ የሚወሰደው እርምጃ የፀጥታውን መደፍረስ ለመቆጣጠርና ሕግና ሥርዓት ለማስከበር የሚያስችል ተመጣጣኝ ኃይል ወይም እርምጃ መሆን ይኖርበታል፤

፫· የክልሉ መንግሥት የፀጥታውን መደፍረስ ለመቆጣጠር የሚያስችሉ መረጃዎችን የመስጠት እና ሁኔታዎችን የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት፤

፬· የሚሰማራው ኃይል በፀጥታው መደፍረስ የተሳተፉ ሰዎችን ለፍርድ ለማቅረብ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ፤

፭· የፀጥታው መደፍረስ በቁጥጥር ሥር ከዋለ ወይም የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል የክልሉ ምክር ቤት የተሠማራው ኃይል ተልዕኮ እንዲያበቃ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥያቄ ካቀረበ የተሰማራው ኃይል ተልዕኮው ያበቃል ።

፮· **ሪፖርት ስለማቅረብ**

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በክልሉ የተሰማራው ኃይል ስለአከናወናቸው ተግባራት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል ።

## *PART ONE*
## *GENERAL*

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "System for the Intervention of the Federal Government in the Regions Proclamation No. 359/2003."

2. *Definition*

In this Proclamation:

1. "Intervention" means a system for intervention in the Regions pursuant to Article 62 (9) of the Constitution and includes measures to be taken in accordance with Article 51 (14) or Article 55 (16) of the Constitution.
2. "Person" means a natural or juridical person.

## *PART TWO*
## *INTERVENTION IN CASE OF DETERIORATING SECURITY SITUATION*

3. *Principle*

The security situation shall be deemed to have been deteriorated where there is an activity that disturbs the peace and safety of the public and the law enforemcement agency and the judiciary of the Region are unable to arrest the security problems in accordance with the law.

4. *Request of the Region*

The State Council or the highest executive organ of the Region shall present its request to the Prime Minister through the Ministry of Federal Affairs where any Region faces a deteriorating security situation and unable to arrest it on its own.

5. *Deployment of Force by the Federal Government*

1. The Prime Minister shall deploy the Federal Police or defense force, or both to arrest the deteriorating security sitaution taking into consideration the gravity of the situation. The force to be deployed shall be under the command of the concerned Federal organ;
2. The force to be deployed and the measures to be taken by same shall be proportionate to enable to arrest the deteriorating security situation and maintain law and order;
3. The Regional Government shall have the responsibility to provide information that enables to arrest the deteriorating security situation and facilitate conditions;
4. The force shall take necessary legal measures to bring to justice those who participated in deteriorating the security situation;
5. The mission of the force deployed shall be terminated where the deteriorating security situation has been arrested or where the highest executive organ of the region or the regional council requests the Prime Minister for such termination;

6. *Report*

The Prime Minister shall present periodic report to the House of Peoples' Representatives on the activities carried out by the forces in the Region.

www.abyssinialaw.com



## ክፍል ሦስት
## በሰብዓዊ መብት መጣስ ምክንያት ስለሚደረግ ጣልቃ ገብነት

፯. *መሠረቱ*

በአንድ ክልል ውስጥ በሕገ-መንግሥቱና ሕገ-መንግሥቱ መሠረት አድርገው በወጡ ሕጎች የተመለከቱትን የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች የመጣስ ድርጊት ሲፈጸምና በሕግ አስከባሪው እና በዳኝነት አካሉ በቁጥጥር ሥር ለማዋል ካልተቻለ የሰብዓዊ መብት መጣስ ድርጊት እንደተፈጸመ ይቆጠራል ።

፰. አጣሪ ቡድን ስለመላክ

፩. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማናቸው ክልል ውስጥ የፌዴራል መንግሥቱን ጣልቃ ገብነት የሚጠይቅ የሰብዓዊ መብት የመጣስ ድርጊት መፈጸሙንና ክልሉ ድርጊቱን ማቆም አለመቻሉ ከሰብአዊ መብት ኮሚሽን ፣ የሰብዓዊ መብት መጣስ ድርጊት ከተፈጸመበት ክልል ተወካዮች ወይም ከሌላ ከማናቸውም ሰው መረጃ ሲደርሰው ጉዳዩን የሚያጣራ ቡድን ወደ ክልሉ ሊልክ ይችላል ። ቡድኑ ከወተካዮች ምክር ቤት የተውጣጡ አባላትን የያዘ ይሆናል ፤

፪. ቡድኑ እንደአስፈላጊነቱ የፌዴራል አስፈጻሚ አካላት ባለሙያዎችን እገዛ ሊጠይቅ ይችላል ፤

፫. ማናቻውም የክልል አካል ከቡዱኑ ጋር የመተባበር ግዴታ ይኖርበታል ።

፱. በቡድኑ ስለሚቀርብ ሪፖርት

፩. ቡድኑ የሰብዓዊ መብት መጣስ ድርጊት ተፈጸሟል በተባለበት ክልል ተገኝቶ ያሰባሰባቸውን መረጃዎች ከራሱ አስተያየት ጋር አጠናቅሮ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚጠናቀር ሪፖርት በክልሉ የተፈጸመውን የሰብዓዊ መብት መጣስ ድርጊት የሚያስረዱ ተጨባጭ ማስረጃዎች፣ የችግሩ ምንጭና ተጠያቂ ሰዎች ፤ የሰብአዊ መብት መጣስ ድርጊቱን ለመቆጣጠር በክልሉ የተደረገውን ጥረት ፣ በክልሉ የተወሰደ እርምጃ እና ክልሉ ድርጊቱን ማቆም የሚችል ወይም የማይችል መሆኑን የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል ።

፲. ጥያቄና ሪፖርት ስለማቅረብ

፩. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ መሠረት ሪፖርት ሲቀርብለት ጉዳዩ የፌዴራል መንግ ሥቱን ጣልቃ ገብነት የሚጠይቅ ሆኖ ያገኘው እንደሆነ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት የጋራ ስብሰባ በመጥራት ጥያቄውን ያቀርባል ፤

፪. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፌዴራል መንግሥቱን ጣልቃ የመግባት አስፈላጊነት ከበቂ ምክንያት ጋር ለጋራ ስብሰበው ሪፖርት ያቀርባል ።

፲፩. *መመሪያ ስለመስጠት*

የጋራ ስብሰባው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲(፪) መሠረት የቀረበለት ሪፖርት ተቀባይነት ያለው ሆኖ ያገኘው እንደሆነ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጋራ ስብሰባው ውሣኔ መሠረት ክልሉ የሰብዓዊ መብት መጣስ ድርጊቱን እንዲያቆም፣ ሰብዓዊ መብት የጣሱትን ሰዎች ለፍርድ እንዲያቀርቡና ሌሎች አግባብነት ያላቸው እርምጃዎች እንዲወስዱ መመሪያ ይሰጣል ።

## *PART THREE*
## *INTERVENTION IN CASE OF VIOLATIONS OF HUMAN RIGHTS*

7. *Principle*

An act of violations of human rights shall be deemed to have been committed where an act is committed in a Region in violation of the provision of the human rights stipulated in the Constitution and laws promulgated pursuant to the Constitution, and the law enforcement agency and the judiciary are unable to arrest such violations of human rights.

8. *Investigating Team*

1. The House of Peoples' Representatives may send a team to the Region for investigation of a case when it receives information from the Human Rights Commission, representatives of such Region or from any other person on the violations of human rights which require the Federal intervention and on the fialure of the region to arrest the acts. The team shall consist of members from the House of Peoples' Representatives;
2. The team may, where necessary, request the assistance of the experts of the Federal Executive organs;
3. Any Regional organ shall have an obligation to cooperate with the team.

9. *Report of the Team*

1. The team shall compile and submit with its recommendations to the House of Peoples' Representatives information gathered within the Region where the alleged acts of the violations of the human rights are committed;
2. The report compiled pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall specify concrete evidence that describes the act of the violations of human rights in the Region, the sources of the problem and persons responsible for it, efforts made and measures taken by the Region to arrest such violations of human rights and whether or not such Region will be able to arrest the act.

10. *Request and Report*

1. The House of Peoples' Representative shall, upon hearing a report submitted to it pursuant to Article 9 of this Proclamation, call a joint session of the House of Peoples' Representatives and the House of the Federation and submit the request to same where it finds that the matter requires the intervention of the Federal Government;
2. The House of Peoples' Representatives shall present a report with justification to the joint sesssion of the necessity of the intervention of the Federal Government.

11. *Giving directive*

Where the joint session is convinced by the report submitted to it pursuant to Article 10 (2) the house of Peoples Representatives shall according to the decision of the joint session, give directives to the Region to arrest the acts of violations of human rights, and bring to justice those who violated such human rights and take other measures as may asmaybe necessary.

www.abyssinialaw.com



## ክፍል አራት
## የሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ አደጋ ላይ በመውደቁ የሚደረግ ጣልቃ ገብነት

፲፪· **መሠረቱ**

በአንድ የክልል መንግሥት ተሳትፎ ወይም ዕውቅና ሕገ-መንግሥቱን ወይም ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ባለማክበር የሚደረግ እንቅስቃሴ ወይም ድርጊት በተለይም፤

፩· በትጥቅ የተደገፈ የአመጽ እንቅስቃሴ ማድረግ፤

፪· ከሌላ ክልል ወይም ከሌላ ክልል ብሔር ፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ጋር የተፈጠሩ ችግሮችን ሰላማዊ ባልሆነ መንገድ መፍታት ፤

፫· የፌዴራሉን ሰላምና ጸጥታ ማናጋት ወይም

፬· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ የተሰጠውን መመሪያ አለማክበር፤

ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣለ እንቅስቃሴ ወይም ድርጊት እንደሆነ ይቆጠራል ።

፲፫· **ስለማጣራትና ውሳኔ ስለመስጠት**

፩· የፌዴሬሽን ምክር ቤት በራሱ አነሳሽነት ወይም ከተወካዮች ምክር ቤት ወይም ከሌላ ከማናቸውም አካል አንድ ክልል ሕገ-መንግሥቱን በመጣስ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ መጣሉ መረጃ ሲደርሰው የቀረቡለትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ አስፈላጊውን ማጣራት ካደረገ በኋላ አደጋው መኖር አለመኖሩን ለመወሰን እንዲሆን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም ሌላ መንግሥታዊ አካል ጉዳዩን አጣርቶ ሪፖርት እንዲያቀርብለት መመሪያ ለማስተላለፍ ይችላል፤

፪· የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፺፫ እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ማናቸውም ክልል ሕገ-መንግሥቱን በመጣስ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ መጣሉ መረጃ ሲደርሰው ጉዳዩን በማጣራት የተፈጠረው አደጋ የፌዴራል መንግሥቱን ጣልቃ መግባት የሚጠይቅ ሆኖ ያገኘው እንደሆነ ጉዳዩን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል ፤

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የሚቀርብ ሪፖርት ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣሉ ምክንያቶች የሚፈቱበት ሰላማዊ መንገድ መተውንና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ የተመለከቱት መፈጸማቸውን የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል ፤

፬· የፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የቀረበለትን ሪፖርት ወዲያውኑ መርምሮ የፌዴራል መንግሥቱ ጣልቃ መግባት አስፈላጊ ሆኖ ያገኘው እንደሆነ ጣልቃ እንዲገባ ያዛል ።

፲፬· **በፌደራል መንግሥቱ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች**

፩· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ (፬) መሠረት የሚሰጥ ትዕዛዝ ሕገ- መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣለውን ሁኔታ ለማስወገድ የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፤

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንዲሁም የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፺፫ እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ይችላል ፤

## *PART FOUR*
## *INTERVENTION WHEN THE CONSTITUTIONAL ORDER IS ENDANGERED*

12. *Principle*

An activity or act carried out by the participation or consent of a Regional Government inviolation of the Constitution or the consitutional order and in particular:

1. armed uprising;
2. resolving conflicts between another Region or Nation, Nationality or People of another Region by resorting to non-peaceful means;
3. distrurbance of peace and security of the Federal Government; or
4. violation of directives given pursuant to Article 11 of this Proclamation;

shall be deemed to have been an activity or act that has endangered the constitutional order.

13. *Investigation and Decisions*

1. The House of the Federation, on its own initaitve or when it receives information from the House of Peoples' Representatives or from any other body that any Region has endangered the Constitutional order by violating the Constitution may, based on the information submitted to it and after having conducted a necessary invstigation, give directives to the Council of Ministers or to other government organ to investigate and report to it in order to decide whether there is danger;
2. Without prejudice to Article 93 of the Constitution, the Council of Ministers shall, when it receives information that any Region in violation of the constitution has endangered the constitutional order, present the matter to the House of the Federation after having carried out its investigation and where it finds it that such danger requires the intervention of the Federal Government;
3. The report to be submitted pursuant to Sub-Article (1) and (2) of this Article shall indicate that the peaceful means to settle the causes which endangered the constitutional order has been left out and the conditions provided for in Article 12 of this proclamation have been met;
4. The House of the Federation shall, after having examined forthwith the report submitted to it pursuant to Sub-Articles (1) and (2) of this Article, order the intervention of the Federal Government where it finds it necessary.

14. *Measures to be taken by the Federal Government*

1. The order to be given pursuant to Article 13 (4) of this Proclamation shall be that which enables to arrest the situation that has endangered the consititutional order;
2. Without prejudice to the generality of Sub-Article (1) of this Article and Article 93 of the consitution, the House of the Federation may take the following measures:

www.abyssinialaw.com



ሀ) እንደችግሩ ክብደት አደጋውን ለማስወገድ የሚያስችል የፌዴራል ፖሊስን ወይም የሀገር መከላከያ ሠራዊትን ወይም ሁለቱንም በክልሉ እንዲያሠማራ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ መመሪያ የመስጠት፣

ለ) የክልሉን ምክር ቤት እና የክልሉን ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል በማገድ ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ የሆነ ጊዜያዊ አስተዳደር እንዲቋቋም የመወሰን፣

፫· ጊዜያዊ አስተዳደሩ በክልሉ የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ይችላል ፡

ሀ) ሕገ–መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ በመጣል የተሣተፉ የክልሉ መንግሥት ባለሥልጣኖች፣ ተሿሚዎች ፡ ተመራጮች፣ የፖሊስና የፀጥታ ኃይል አባላት እና ሌሎች ሰዎችን ለፍርድ እንዲቀርቡ የማድረግ፣

ለ) በክልሉ ሕገ–መንግሥታዊ ሥርዓቱ ተጠብቆ የክልሉ መንግሥት መደበኛ ሥራውን የሚጀምርበትን ሁኔታ በአፋጣኝ የማመቻቸት፣

፬· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) (ሀ) መሠረት በተወሰደው እርምጃ ምክንያት የክልል አስፈጻሚ አካል አቅም የተጓደለ እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በሚያቀርበው የውሣኔ ሀሳብ መሠረት የፌዴራል መንግሥቱን ሠራተኞች በጊዜያዊነት በመመደብ መደበኛ ሥራው እንዲቀጥል ማድረግ ይችላል፤

፭· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሀ) በፌዴራል ፖሊስ ወይም በመከላከያ ኃይል የሚወሰድ እርምጃ ሕገ–መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣለውን ሁኔታ ለማስወገድ በሚያስችል መጠን መሆን ይኖርበታል ፡

፮· ሕገ–መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣለው ሁኔታ መወገዱን የፌዴሬሽን ምክር ቤት ካመነ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፭ (፫) የተደነገገው የጊዜ ገደብ ከመድረሱ በፊት ጊዜያዊ አስተዳደሩ የሚያበቃበትን የጊዜ ገደብ በመወሰን ለሚመለከታቸው አካላት መመሪያ ያስተላልፋል ።

፲፭· <u>ስለጊዜያዊ አስተዳደሩ</u>

፩· ጊዜያዊ አስተዳደሩ ሕገ–መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣለውን ሁኔታ ለማስወገድ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳል።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ጊዜያዊ አስተዳደሩ ለክልሉ ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል የተሰጡት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ። በተለይም ጊዜያዊ አስተዳደሩ፤

ሀ) አስፈጻሚ አካሉን ይመራል ፤ ያስተባብራል፤

ለ) የጊዜያዊ አስተዳደሩን ኃላፊዎች ይመድባል፤

ሐ) ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፤

መ) አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በክልሉ ምርጫ የሚከናወንበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ሠ) የክልሉን ዕቅድና በጀት ያፀድቃል፤

ረ) በፌዴራል መንግሥቱ የሚሰጡ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል።

፫· ጊዜያዊ አስተዳደሩ በክልሉ የሚቆየው ከሁለት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ነው ። ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመቆያ ጊዜውን ከ፮ ወር ላልበለጠ ጊዜ ለማራዘም ይችላል ።

(a) To give directives to the Prime Minister to deploy the Federal Police or national defense force or both, depending on the seriousness of the problems, to enable arrest the danger;

(b) to decide to set up provisional administration that is accountable to the Federal Government by suspending the State Council and the highest executive organ of the Region.

3. The Provisional Administration may take the following measures in the region:

(a) To bring to justice the Regional Government officials, appointees, officials elected by the People, members of the police and security force, and other persons responsbile for the danger of the constitutional order;

(b) To speedily facilitate conditions for the regional Government to resume its office by restoring the constitutional order;

4. The Prime Minister may, upon the recommendation of the Ministry of Federal Affairs, assign temproraily the Federal Government personnel for the resumption of regular activties of the region where the capacity of the executive organ of the Region is impaired by the measures taken pursuant to Sub-Article 3 (a) of this Article;

5. The measures to be taken by the Federal police or the defense force pursuant to Sub-Article 2(a) of this Article shall be proportionate to enable to arrest the situation that has endangered the constitutional order;

6. The House of the Federation shall, where it believes that the situation that endangered the constitutional order has been arrested, give directives to the concerned organs determining the expiry period of the Provisional Administration period to the period mensioned in Article 15 (3).

15. *Provisional Administration*

1. The Provisional Administration shall take measures that enable to arrest the situation that has endangered the constitutional order;

2. Without prejudice to the generality of Sub-Article (1) of this Article, the Provisional Administration shall have powers and duties given to the highest executive organ of the Region, and shall in particular;

(a) lead and coordinate the executive organ;

(b) assign the Heads of the Provisional Administration;

(c) ensure the enforcement of law and order;

(d) facilitate conditions for conducting election in the Region in accordance with relevant law;

(e) approve a plan and budget of the Region;

(f) carry out other duties to be entrusted to it by the Federal Government.

3. The Provisional Administration shall stay in the region for a period not exceeding two years; however, the House of the Federation may, where necessary, extend the period for not more than six months.

www.abyssinialaw.com



## ፲፮· ሪፖርት ስለማቅረብና ስለክትትል

፩· ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክልሉ ስለሚገኝበት ሁኔታ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በየሦስት ወሩ ሪፖርት ያቀርባል፤

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ በየፌዴሬሽን ምክር ቤት ሲጠየቅ በማናቸውም ጊዜ ሪፖርት ያቀርባል ፤

፫· የፌዴሬሽን ምክር ቤት በክልሉ ስላለው ሁኔታ ጥናትና ግምገማ ለማድረግ የራሱን ቡድን በመላክ የሚገመገም በትን ስልት ይቀይሳል ። በደረሰበት የጥናትና የግምገማ ውጤት መሠረት የእርምት እርምጃ መውሰድ የሚጠይቁ ጉዳዮች ከተገኙ መመሪያ ያስተላልፋል ።

## ፲፯· ለሕዝብ ስለማሳወቅ

፩· የፌዴሬሽን ምክር ቤት እና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ አደጋ ላይ ስለጣለው ሁኔታ ፤ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ስለሰጠው ውሣኔ እና በክልሉ ስላለው ወቅታዊ ሁኔታ ለሕዝብ መግለጫ ይሰጣሉ፤

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ የክልሉ ሕዝብ ስለሁኔታው መረጃ የሚያገኝበትና ሐሳብ የሚሰጥበት መድረክ በየወቅቱ መዘጋጀት ይኖርበታል ። በተዘጋጀው መድረክ ላይ የቀረቡ የሕዝብ ሀሳቦች ተጠናቅረው ለፌዴሬሽን ምክር ቤትና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲደርሱ ይደረጋል ።

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፲፰· የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም የፌዴራል ወይም የክልል ባለሥልጣን፤ ሠራተኛ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት።

## ፲፱· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

## 16. *Reporting and Follow-up*

1. The Prime Minister shall quarterly submit report on the conditions of the Region to the House of the Federation;
2. Without prejudice to Sub-Article(1) of this Article the Prime Minister shall, on request of the House of the Federation, present a report at any time;
3. The House of the Federation shall devise its own mechanism to conduct study and evaluation within the Region sending its own team, and give directives where there are matters that requires corrective measures based on the findings of the study and evaluation.

## 17. *Publication*

1. The House of the Federation and the Prime Minster shall issue statements to the public about the situation that endangered the constitutional order, the order given by the House of the Federation and current situation of the Region;
2. Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, a forum shall be held peridically to enable the public within the Region to have access to information about the situation and give opinions thereon. The public opinions expressed on such forum shall be compiled and submitted to the House of the Federation and the Council of Ministers.

## *PART FIVE*
## *MISCELLANEOUSE PROVISIONS*

## 18. *Duty to Cooperate*

Any authority of the region, worker or any other person has the obligation to cooperate for the implementation of this Proclamation.

## 19. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force at the date of its publication in the Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 10th day of July, 2003.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE